Seattle Public Schools

# የሲያትል የህዝብ ትምህርት ቤቶች ዘላቂ መፍትሄዎች

ሲያትል የህዝብ ትምህርት ቤቶች፣ለእያንዳንዱ ተማሪ ጥራት ያለው ትምህርት እንዲገኝ እና ያጋጠመውን ከፍተኛ የሆነ የበጀት እጥረት ለመፍታት ዘላቂ መፍትሄ ለማምጣት ተልእኳችንን በመጠበቅ ላይ እንገኛለን።

**ግምት ውስጥ እንዲገባ የቀረበ ምክረሃሳብ: በ2025-26 አራት አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶችን መዝጋት እና ማዋሃድ**

በዚህ ፕሮፖዛል Sanislo፣Stevens፣Sacajawea እና North Beach ተዘግተው ከአጎራባች ትምህርት ቤቶች ጋር ይቀላቀላሉ።ይህ የትምህርት ቤት ማህበረሰቦችን አንድ ላይ የሚያቀይ እና ጠንካራ እና የተዋሃዱ ትምህርት ቤቶችን ይፈጥራል።

**ማዋሃድ የትምህርት ጥራትን እንዴት ያረጋግጣል**

ትምህርት ቤቶችን በማዋሃድ፣የሲያትል የሕዝብ ትምህርት ቤቶች የፋይናንስ መረጋጋታችንን በማጠናከር የተማሪዎችን የትምህርት ግብአቶች ተደራሽነት ያሳድጋል። እነዚህ ሀብቶች የሚከተሉትን ያካትታሉ:

- የላቀ ትምህርት፣ ስነ ጥበባት፣ሙዚቃ እና የSTEM እድሎች
- የተስፋፋ ማህበራዊ-ስሜታዊ እና አእምሯዊ ጤና ተደራሽነት እና ድጋፍ
- አጠቃላይ የልዩ ትምህርት አገልግሎቶች

**የመዝጋት እና የማዋሃድ መስፈርቶች**

- **የህንፃው ሁኔታ**: የእያንዳንዱ ትምህርት ቤት የመዋቅራዊ እና የስርዓት ጥራት ደረጃ ተሰጥቷል፤ እነዚህ ደረጃዎች ከ 1.00 እስከ 5.00 ሲሆኑ 1.00 ማለት በጣም ጥሩ፣5.00ማለት ደግሞ አጥጋቢ አይደለም ማለት ነው።
- **የመማሪያ አካባቢ**: ትምህርት ቤቶች የትምህርት እና የደህንነት ፍላጎቶችን  የሚያሟሉ ተስማሚ፣ተለዋዋጭ የመማሪያ ቦታዎች ተገምግመዋል፤ 1 = በጣም ጥሩ፣ 5 = የማይመች።
- **ተማሪዎችን የማገልገል አቅም**:ትምህርት ቤቶች የሲያትል የሕዝብ ትምህርት ቤቶችን የክፍል መጠን፣ልዩ ፕሮግራሞችን እና አስፈላጊ ግብዓቶችን የመደገፍ ችሎታቸው ላይ ተገምግመዋል።
- **የክልሉ የምዝገባ ፍላጎቶች**:ይህን ሙሉ በሙሉ ማዋሃድ የሚል ምክረሃሳብ የቀረበው የክልሉ የምዝገባ አዝማሚያዎች እና ከአጎራባች ትምህርት ቤቶች ጋር ያለው ቅርበት ታሳቢ ተደርጎ ነው።

---